የኢትዮጵያ
ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን
ETHIOPIAN HUMAN
RIGHTS COMMISSION

ቁጥር
Ref No. ኢሰመኮ/3.4/14/2016

ቀን
Date የካቲት 21 2016

ለኢፌዴሪ የፍትህ ሚኒስቴር

<u>አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ</u>

<u>ጉዳዩ፡ የኤፌዴሪ ረቂቅ የሽግግር ፍትህ ፖሊሲ ሰነድ ላይ ኢሰመኮ ያደረገውን አስተያየት ማስተላለፍን ይመለከታል</u>

የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን (ኢሰመኮ) በፌዴራል ሕገ መንግሥቱ መሠረት ነጻ ፌዴራላዊ መንግሥት አካል ሆኖ በአዋጅ ቁጥር 210/1992 (በአዋጅ ቁጥር 1224/2012 እንደተሻሻለው) የተቋቋመና ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ተጠሪ የሆነ ለሰብአዊ መብቶች መስፋፋት፣ መከበር እና ጥበቃ የሚሠራ ብሔራዊ የሰብአዊ መብቶች ተቋም ነው፡፡ ኢሰመኮ በዚህ አዋጅ መሰረት ከተሰጡት ዝርዝር ተግባርና ኃላፊነቶች ውስጥ ሰብአዊ መብቶች ላይ ተጽእኖ የሚኖራቸውን ረቂቅ ህጎችና ፖሊሲዎችን መመርመርና አስተያየት መስጠት ይገኝበታል፡፡

ኢሰመኮ የሽግግር ፍትህ የባለሙያዎች ሥራ ቡድኑ የኢትዮጵያን የሽግግር ፍትህ ፖሊሲ ማዕቀፍ በማዘጋጀት ሂደት ላይ ላደረገው ትልቅ አስተዋጽኦ ያለውን አድናቆት እየገለጸ፣ በዚህ ደብዳቤ፣ በኤፌዴሪ ረቂቅ የሽግግር ፍትህ ፖሊሲ ሰነድ ላይ ያደረግነውን የግምገማ አስተያየት በአክብሮት እናስተላልፋለን።

ኢሰመኮ በተቋቋመበት አዋጅ መሰረት ዓለም አቀፍ፣ አህጉራዊ፣ እና ሃገር አቀፍ የሰብአዊ መብቶች ድንጋጌዎችን በመጠቀም ለሕዝብ በቀረበው ረቂቅ የሽግግር ፍትህ ፖሊሲ ላይ አጠቃላይ ትንተና አካሂዷል፣ እንዲሁም የሰብአዊ መብቶች መርሆዎችን ማጎልበት የሚችሉ ገንቢ አስተያየቶችንም አቅርቧል። በተጨማሪም ግምገማችን በሽግግር ፍትህ ሂደት ውስጥ ሊከበሩ ከሚገባቸው እንደ አካታችነት፣ አሳታፊነት፣ ቅቡልነት እና መሰል መርሆዎች እንዲሁም የተለየ ትኩረት ከሚሹ ጉዳዮች አንጻር የተደረገ ነው። እንዲሁም እንደ ተጠያቂነትን የማስፈን፣ የሽግግር ፍትህ ተቋማትን ስራ የማሰናሰል፣ እና ሃገራዊ አውድን መከተል ያሉ የሽግግር ፍትህ ሂደት የሚመራባቸው ቁልፍ ጉዳዮችን በሚመለከት ሰነዱ የተከተለውን አካሄድ በመመርመር የተሰጠ አስተያየትንም ይጨምራል። ይህ የግምገማ አስተያየት የሽግግር ፍትህ ፖሊሲ ማዕቀፍን በማርቀቅ ረገድ ለሚደረጉ ቀጣይ ጥረቶች አስተዋጽኦ ያደርጋል ብለን ተስፋ እናደርጋለን።

ከዚህ ደብዳቤ ጋር ተያይዞ በረቂቅ ፖሊሲ ሰነዱ ላይ አጠቃላይ አስተያየት የሚያቀርበውን ሰነድ ያገኛሉ። ኢሰመኮ በዚህ ታላቅ ሃገራዊ ጉዳይ ላይ ከኢፌዲሪ የፍትህ ሚኒስቴር ጋር ቀጣይነት ያለው ትብብር ለማድረግ ያለውን ዝግጁነት በዚህ አጋጣሚ በድጋሚ ይገልጻል።

ከሰላምታ ጋር፣

ዳንኤል በቀለ (ዶ/ር)
የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች
ኮሚሽን ዋና ኮሚሽነር


www.ehrc.org

ስልክ / Phone
+251-11550 4031

ፋክስ / Fax
+251-11 550 4125

ኢሜል / Email
info@ehrc.org

ፖስታ ሳጥን ቁጥር / P. O. Box
1165 አዲስ አበባ

አድራሻ / Address
ሰንሻይን ታወር ቁጥር 5፣ መስቀል አደባባይ አለፍ ብሎ በሌ መንገድ ፣ ሀያት ሬጀንሲ ሆቴል አጠገብ፣ አዲስ አበባ
Sunshine Tower No. 5, Meskel Square, on Bole Road next to Hyatt Regency Hotel, Addis Ababa